# የገንዘብ ሚኒስቴር

## ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ማሻሻያ ስለሚሰጥ ማበረታቻ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 941/2015

**የገንዘብ ሚኒስቴር**
**ጥር, 2015 ዓ.ም**

## ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ማሻሻያ ለሚሰጥ ማበረታቻ

## <u>አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 941/2015</u>

ነባር ኢንቨስትመንታቸውን የሚያስፋፉ ወይም የሚያሻሽሉ ባለሀብቶች ከማስፋፊያው ወይም ከማሻሻያው የሚያገኙት ተጨማሪ ገቢ ከኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ጋር የተያያዘውን ሰንጠረዥ መሠረት በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት እንደሚያገኙ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 5 የተደነገገ በመሆኑ፤

ለነባር ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ የሚውሉ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ለማስገባት የሚቻለው ባለሃብቱ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ማስረጃዎችን ሲያቀርብ እንደሚሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 12(5) የተመለከተ ስለሆነ፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 5 እና 12(5) የገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተሰውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1 <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ መመሪያ “ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ማሻሻያ ለሚሰጥ ማበረታቻ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 941/2015“ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

በአዋጁ እና በደንቡ ለቃላት እና ሀረጎች የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ:

1/ “አዋጅ“ ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው፡፡

2/ “ደንብ“ ማለት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 517/2014“ ነው፡፡

3/ “ነባር ድርጅት“ ማለት የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ኖሮት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ድርጅት ነው፡፡

4/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚሰጥ <u>ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ</u>

3. <u>የማበረታቻው አጠቃቀም</u>

1/ ነባር ድርጅትን የማስፋፋት ወይም የማሻሻል ስራ ያከናወነ ድርጅት ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለዉ በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) ሊደረስበት የሚችል የነባር ድርጅትን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም በሚከተለው መጠን የሚያሳድግ ኢንቨስተር፤

(i) ከ50-70% ድረስ የሚያሳድጉ ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በእድገቱ ምክንያት ባገኙት ገቢ ላይ ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር 60%፤

(ii) ከ71-90% ድረስ የሚያሳድጉ ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ጊዜ ወስጥ በእድገቱ ምክንያት ባገኙት ገቢ ላይ ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር 80%፤

(iii) ከ90% በላይ የሚያሳድጉ ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው ጊዜ ወስጥ በዕድገቱ ምክንያት ባገኙት ገቢ ላይ ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር 100%፤

ለ) ለነባር ድርጅት አዲስ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መስመር በመጨመር ምርትን ወይም አገልግሎትን በዓይነት ወይም በመጠን ቢያንስ መቶ በመቶ የሚያሳድግ ኢንቨስተር ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ስተመለከተው ጊዜ በማሻሻያው ምክንያት በተገኘው ገቢ ላይ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል፡፡

2/ በደንቡ አንቀጽ 5(2) በተደነገገው መሰረት ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የተሰጠው ተጨማሪ ከንግድ ትርፍ ግብር ነጻ የመሆን መብት ተፈጻሚ የሚሆነው ከማሻሻያው ወይም ከማስፋፊያው ለተገኘው ተጨማሪ ገቢ ብቻ ነው፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) አፈጻጸም ማናቸውም ኢንቨስተር ነባር ድርጅት የማስፋፋት ስራ በማከናወኑ የመብቱ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ሊደረስበት የሚችለውን የነባር ድርጅቱን የማምረት አቅም የማስፋፋቱ ስራ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ በመጠን ከ50% ከፍ አድርጎ ሲገኝ ነው፡፡

## 4. <u>የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ሲሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች</u>

1/ ማናቸውም ኢንቨስተር ነባር ድርጅትን በማስፋፋት ወይም በማሻሻል የሚሰጠው ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለው የሚከተሉት መስፈርቶችን ሲያሟላ ይሆናል፣

ሀ) ድርጅቱ ቢያንስ ለ36 ወራት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ ተሰማርቶ የቆየ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ) ነባሩን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ስራ ለማስፋፋት፣ የአመራረት ዘይቤውን ለማዘመን፣ አዲስ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ወይም የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን አይነት ለማብዛት ያዋለውን መዋዕለ ንዋይ የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት፣

ሐ) ከማስፋፊያው መጠናቀቅ በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያመረተውን ወይም የሰጠውን አገልግሎት መጠን የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት፣

መ) ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ሆኖ የቆየ ከሆነ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ሆኖ በቆየባቸው ዓመታት በታክስ ሕጎች በተደነገገው መሰረት የገቢ ማስታወቅ ግዴታውን ሲወጣ የቆየ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

2/ በደንቡ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሰረት የግብር እፎይታ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የግብር እፎይታው ተጠቃሚ ከሆነ በኋላ የተሰማራበትን ኢንቨስትመንት ዘግቶ ተመልሶ የዕፎይታ ጊዜ በሚያሰጥ ኢንቨስትመንት ላይ ከተሰማራ ቢያንስ በዘጋው ኢንቨስትመንት የተጠቀመበትን የእፎይታ ጊዜ ለሚያክል ጊዜ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም የግብር ዕፎይታ ተጠቃሚው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ የተዘጋው ድርጅት ባለአክሲዮን አዲስ ከተቋቋመው ድርጅት አክሲዮኖች መካከል ከ50% በላይ የሚሆኑት አክሲዮኖች ባለቤት ከሆነ አዲስ የተቋቋመው ድርጅት የተዘጋው ኢንቨስትመንት የተጠቀመበትን የዕፎይታ ጊዜ ለሚያክል ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር ዕፎይታ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

4/ የተሰማራበትን ነባር ድርጅት የዘጋ ባለሃብት ከንግድ ትርፍ ግብር ነጻ የመሆን ማበረታቻ ሲጠይቅ የሚችለው በማስፋፊያ ወይም በማሻሻያ መልክ ሳይሆን እንደ አዲስ ኢንቨስትመንት ሲሆን ይገባል፡፡

5/ በደንቡ አንቀጽ 19 1(ለ) እና አንቀጽ 20 በተደነገገው መሠረት ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ባለሀብቱ ከንግድ ትርፍ ግብር ነጻ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በመመርመር ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ አለባቸው፡፡

## 5. <u>የሂሳብ መዝገብ አያያዝ</u>

1/ ባለሀብቱ ከማሻሻያው ወይም ከማስፋፊያው የተገኘውን ገቢ እና የተደረገውን ወጪ ለይቶ በሂሳብ መዝገብ ማሳየት አለበት፡፡

2/ ባለሀብቱ ከማስፋፊያው የተገኘውን ገቢ እና ለማስፋፊያው የተደረገውን ወጪ ለይቶ የሚያሳየው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 76 የተደነገገውን የማከፋፈል ደንብ በመጠቀም ሲሆን ይገባል፡፡

## 6. <u>የማበረታቻው ተፈፃሚነት የሚጀምርበት ጊዜ</u>

ለማስፋፊያ ወይም ለማሻሻያ የሚሰጠው ማበረታቻ ተፈፃሚነት መቆጠር የሚጀምረው ባለሃብቱ በማሻሻያው ወይም በማስፋፊያው ምክንያት ካፒታሉን በማሳደግ የተሻሻለውን የንግድ ስራ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

# ለነባር ድርጅት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ የካፒታል ዕቃዎችን <u>እና የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ስለማስገባት</u>

## 7. <u>ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለመሆን ሊሟሉ የሚገባቸዉ መስፈርቶች</u>

1/ የማሻሻያ ወይም የማስፋፊያ ስራ የሚያከናውን ባለሃብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለዉ ሲደረስበት የሚችል የነባር ድርጅትን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ ሃምሳ በመቶ በመጠን የሚያሳድግ ወይም የነባር ድርጅትን አዲስ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መስመር በመጨመር ምርትን ወይም አገልግሎትን ቢያንስ መቶ በመቶ በዓይነት ለማሳደግ ወይም በሁለቱም ለማሳደግ የተዘጋጀ መሆኑን የሚያሳይ እቅድ ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

2/ ድርጅቱ ባለው ልዩ የስራ ባህሪ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል መሆኑ እና ለማስፋፊያው ወይም ለማሻሻያው ስራ እንዲውሉ ወደአገር የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች የድርጅቱን አሰራር ለማዘመን፣ ምርታማነቱን ለማሳደግ፣ የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን ዓይነት ለማብዛት የሚውሉ መሆኑ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ሲረጋገጥ የገንዘብ ሚኒስቴር የካፒታል ዕቃዎቹ በልዩ ሁኔታ ወደአገር እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተመለከተው ባለሀብቱ ባቀረበው እቅድ መሠረት የማስፋፋት ወይም የማሻሻል ስራውን ካላከናወነ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደአገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ ቀረጥ እና ታክሱን እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

# ክፍል አራት

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 8. ተጠያቂነት

1/ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት መሠረት ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚሰጥ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ለድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ የተጋነነ፣ የሀሰት ወይም አሳሳች እንዲሁም የተጭበረበረ ማስረጃን በማቅረብ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የተሰጠው ተጨማሪ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚ የሆነ ኢንቨስተር፣ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 118 (2) መሰረት የሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢንቨስተሩ የተጋነነ፣ የሀሰት፣ አሳሳች ወይም የተጭበረበሩ መረጃዎችን በማቅረብ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ለተደረገባቸው ዓመታት ተገቢውን ግብር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2/ ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ጋር በተገናኘ የተጋነነውን፣ አሳሳች የሆነዉን ወይም የተጭበረበረዉን ሰነድ ያዘጋጀ ወይም እንዲዘጋጅ የተባበረ ኦዲተር በታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 48 በተመለከተው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ለተመለከተው ጥፋት ሃላፊ ሆኖ በተገኘው ኦዲተር ላይ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ እና አዘገጃጀት አዋጅ በተደነገገው መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ለኢትዮጵያ የሂሳብ እና ኦዲት ቦርድ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 9. ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የድህረ ገጽ አድራሻ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ጥር፣ 2015 ዓ.ም.**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስትር**